በፓስተር ማስረሻ መኮንን

ማቴዎስ 28 (Matthew)
19-20፤ እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችኋቸው፥ ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ እያስተማራችኋቸው ደቀ መዛሙርት አድርጓቸው፤ እነሆም እኔ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ሁልጊዜ ከእናንተ ጋር ነኝ።
ማር 3:13
ደቀ መዝሙር ማለት:- ከመምህሩ የተማረ
:- ልክ እንደ መምህሩ
በዚህ ዘመን ሁሉ ነገር ተመሳሳይ ከመሆኑ የተነሳ
መልከሙን ከክፉ ለመለየት እንቸገራለን ።
ዛሬ ሰይጣን ሁሉን መንፈሳዊ አስመስሎ እውነተኛ የሆኑ ክርስቲያኖችን እኪያስት ይደርሳል።
ስለዚህ ዛሬ በእውነተኛው መንገድ እንደ እግዚአብሔር ቃል ደቀ -መዝሙር ያልሆኑ ሰዎች በቤተ ክርስቲያን አሉ፣ የእግዚአብሔርንም ስራ ያደናቅፋሉ፣ ሌሎችም እውነተኛ ደቀ መዝሙር እንዳይሆኑ እንቅፋት ይሆናሉ። ደቀ መዝሙርነት ለዓለም ብርሀን እና ጨው መሆን ነው፣ የተጠራነው በሁሉ ስፍራ
የእውነተኛ ደቀ -መዝሙር መገለጫዎች (መለያው): -
1ኛ, ከመምህሩ የተማረ
ሉቃስ 10 (Luke)
41፤ ኢየሱስም መልሶ፡— ማርታ፥ ማርታ፥ በብዙ ነገር ትጨነቂአለሽ ትታወኪማለሽ፥
42፤ የሚያስፈልገው ግን ጥቂት ወይም አንድ ነገር ነው፤ ማርያምም መልካም ዕድልን መርጣለች ከእርስዋም አይወሰድባትም፡ አላት።
**** ቃሉን በሚገባ የሚያጠና***
የማርያም በጌታ ዘንድ እጅግ ተቀባይነት ነበረው።
ዛሬ እናገለግላለን እያልን ከምንባክን ይልቅ በእግሩ ስር ተቀምጠን የምንሰማውን ይፈልጋል።
#ማርታ ቤቷን ጓዳዋን ከፈተች ማርያም ግን ልቧን ከፈተች።
2ኛ, ሁሉን ትቶ ጌታን መከተል።
ማርቆስ 10 (Mark)
21፤ ኢየሱስም ወደ እርሱ ተመልክቶ ወደደውና፡— አንድ ነገር ጐደለህ፤ ሂድ፥ ያለህን ሁሉ ሽጠህ ለድሆች ስጥ፥ በሰማይም መዝገብ ታገኛለህ፥ መስቀሉንም ተሸክመህ፡ ና፥ ተከተለኝ፡ አለው።
ዛሬ በሙሉ ልብ ጌታን እንዳንከተል የሚጎትተን ፣የከበደን ነገር መን የሆን?
እውነተኛ ደቀ መዝሙር ግን መተው የሚገባውን ለጌታው ሲል ትቶ ይከተላል።
3ኛ, ራሱን የጣለ (ራሱን የካደ)።
ዕብራውያን 11 (Hebrews)
35፤ ሴቶች ሙታናቸውን በትንሣኤ ተቀበሉ፤ ሌሎችም መዳንን ሳይቀበሉ የሚበልጠውን ትንሣኤ እንዲያገኙ እስከ ሞት ድረስ ተደበደቡ፤
36፤ ሌሎችም መዘበቻ በመሆንና በመገረፍ ከዚህም በላይ በእስራትና በወኅኒ ተፈተኑ፤
37፤ በድንጋይ ተወግረው ሞቱ፥ ተፈተኑ፥ በመጋዝ ተሰነጠቁ፥ በሰይፍ ተገድለው ሞቱ፥ ሁሉን እያጡ መከራን እየተቀበሉ እየተጨነቁ የበግና የፍየል ሌጦ ለብሰው ዞሩ፤
38፤ ዓለም አልተገባቸውምና በምድረ በዳና በተራራ፥ በዋሻና በምድር ጕድጓድ ተቅበዘበዙ።
ደቀ - መዝሙርነት ራስን ከመካድ ይጀምራል።
ለእኛ ስለሞተው ጌታ መኖር ማለት ነው።
***ራሱን የካደ ክርስቲያን ለጌታው ፈቃድ ብቻ የኖራል።***

ዛሬ ክርስቲያኑ ራሱን ካለመካዱ የተነሳ በትዳሩ፣ በአገልግሎቱ ፣ በስራው፣
4ኛ, መስቀሉን ለመሸከም የፈቀደ።
ማቴዎስ 16 (Matthew)
24፤ በዚያን ጊዜ ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ እንዲህ አለ፡— እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር፥ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ተሸክሞ ይከተለኝ።
ስለወንጌል እውነት ብሎ የሚመጣበትን መከራ ሁሉ ለመቀበል የተዘጋጀ ማንነት።
ዛሬ ፈተናው ወይም መከራው የተለየ ሊሆን ይችላል ፣ ማነው ዛሬ መስቀሉን ለመሸከም የተዘጋጀ።
5ኛ, የመምህሩን ፈለግ የሚከተል።
ዮሐንስ 4 (John)
34፤ ኢየሱስም እንዲህ አላቸው፡— የእኔስ መብል የላከኝን ፈቃድ አደርግ ዘንድ ሥራውንም እፈጽም ዘንድ ነው።
ጌታ ለሊቱን ሁሉ ይፀልይ ነበር፣ ጌታ ብዙ መንፈሳዊ ፈለግን አሳይቶን ሔዷል፣ ማነው ዛሬ የጌታን ፈለግ የሚከተል? ማነው ዛሬ ጊዜውን ለጌታ የሚሰጠው? ማነው ዛሬ የታዘዘውን ወንጌልን የሚሰብክ።
ዮሐንስ 13 (John)
34፤ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ፥ እንደ ወደድኋችሁ እናንተ ደግሞ እርስ በርሳችሁ ትዋደዱ ዘንድ አዲስ ትእዛዝ እሰጣችኋለሁ።
35፤ እርስ በርሳችሁ ፍቅር ቢኖራችሁ፥ ደቀ መዛሙርቴ እንደ ሆናችሁ ሰዎች ሁሉ በዚህ ያውቃሉ።
በዚህም ዘመን ፍቅራችንን በተግባር በመግለፅ፣ ያለንን በማካፈል፣ ሌላው በመኖር፣ ስለወንድሞቻችን በመፀለይ፣ ደቀ - መዝሙርነታችንን ማሳየት አለብን።
6ኛ, ሁል ጊዜ የተላከ መሆኑን የሚያውቅ።
ሉቃስ 5 (Luke)
10፤ እንዲሁም ደግሞ የስምዖን ባልንጀሮች የነበሩ የዘብዴዎስ ልጆች ያዕቆብና ዮሐንስም ተደነቁ። ኢየሱስም ስምዖንን፡— አትፍራ፤ ከእንግዲህ ወዲህ ሰውን የምታጠምድ ትሆናለህ፡ አለው።
ጌታ ይርዳን .........
ይቀጥላል .........